ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

---

# አቶ ኦሞት "ካፈርኩ አይመልሰኝ" አሉ

## "አኬልዳማ ቁጥር ሁለት" ሊዘጋጅ ነው

አቶ ኦሞት ኦባንግ ራሳቸው በጠሩት ግምገማ፣ ራሳቸውን አስገምግመው ከፓርቲው ሊቀመንበርነታቸው መነሳታቸው የንጽህናቸው ውጤት መሆኑን አሰታወቁ። ፕሬዚዳንቱ "እኔን በተመለከተ የተነሳ ምንም ነገር የለም" ማለታቸው ግምገማው ላይ የነበሩ፣ የግምገማው ሙሉ መረጃ ያላቸውንና ስለ ክልሉ በቂ ግንዛቤ ያላቸው ክፍሎች የፕሬዚዳንቱን ንግግር እንዳስገረመ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት አስታወቀ።

አቶ ኦሞት ኦባንግ ከአሜሪካ ሬዲዮ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል ጋር ያካሄዱት ቃለ ምልልስ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" እንደሆነ ከክልሉ የተሰበሰቡ መረጃዎች አመልክተዋል። በቃለ ምልልሱ ፕሬዚዳንቱ እሳቸውን አስመልክቶ ሰሞኑን ሲዘገቡ የነበሩትን ዜናዎች ሲያስተባብሉ ከፓርቲው ሊቀመንበርነታቸው መነሳታቸውን ግን አምነዋል። አነጋጋሪ የሆነው ግን የፓርቲውን ሊቀመንበርነታቸውን ያጡት በግምገማ ወቅት ምንም ጥፋት ስላልተገኘባቸው እንደሆነ አድርገው ማቅረባቸው ነው።

ከፕሬዚዳንትነት ስልጣን ይልቅ የፓርቲ ሊቀመንበርነት ትልቁ የስልጣን እርከን በሆነበት አገር ውስጥ ከፓርቲው ሊቀመንበርነታቸው እንዲወርዱ መደረጋቸውን ያመኑት አቶ ኦሞት በፕሬዚዳንትነት ወንበራቸው ለስድስት ወር እንዲቀመጡ ስለመወሰኑ "የሚታወቅ ነገር የለም" ከማለት ውጭ ማስተባበያ አንዳላቀረቡ የጋራ ንቅናቄው የሚዲያ ክፍል ገልጿል።

የፓርቲያቸውንና የመንግስታቸውን የአምስት ወር የሥራ ክንውን የሚመረምር ግምገማ መካሄዱን ያልሸሸጉት አቶ ኦሞት ግምገማውን የመሩት እሳቸው መሆናቸውን ተናግረዋል። በግምገማው ላይ ከፌደራል መንግስት የተወከሉት ሁለት ባለስልጣናት ከመታዘብ የዘለለ ስራ እንዳልነበራቸው አስረድተዋል። አያይዘውም ባለስልጣናቱ የሚያከራክር ጉዳይ ሲፈጠር ልምዳቸውን ከማካፈል ውጪ በክልሉ ጉዳይ እንደማያገባቸው በመጠቆም ህወሃት በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ በማሳየት ውለታቸውን አጠናክረዋል።

**የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ የማስተባበያ መድረክ ያዘጋጀላቸው አቶ ኦሞት መስቀለኛ ጥያቄ አልቀረበላቸውም። እሳቸውን አስመልክቶ የተዘገቡ ጉዳዮች በየተራ የቀረቡላቸው ፕሬዚዳንቱ፣ በክልሉ ስለተንሰራፋው ሙስና ተጠይቀው "በክልላችን ስላለው የስነምግባር ችግር" በማለት ጉዳዩን አቃለው ሲመልሱ፣ ከክልሉ በሙስና ባከነ ስለተባለው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብና የሰላም ችግር በቂ ማብራሪያ እንዲሰጡ አልተጋበዙም።**

በንባብ መልክ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች ለማስተባበያነት የተጠቀሙት አቶ ኦሞት በክልሉ መሬት ስለወሰዱ ባለሃብቶች ሲናገሩ 707 የሚሆኑት ያገርቤት ባለሃብቶች መሆናቸውን ከመግለጽ ውጭ በክልሉ በከፍተኛ ደረጃ መሬት እየተቀራመቱ ስላሉት ክፍሎች ያሉት ነገር የለም። **የጋራ ንቅናቄያችን ባለው መረጃ በክልሉ መሬት የወሰዱት ሰባ ከመቶ በላይ የትግራይ ሰዎች ናቸው።**

በከፍተኛ ደረጃ ሰፋፊ መሬት የወሰዱት አምስት ባለሃብቶችን በተመለከተ ውለታውም ሆነ የመሬት መስጠቱ ሂደት በፌደራል መንግስት መከናወኑን ፕሬዚዳንቱ ይፋ በማድረግ ቀደም ሲል የሸፈኑትን የህወሃትን ጣልቃ ገብነት ይፋ አድርገዋል። **ፕሬዚዳንቱ የክልሉን ደን እያስጨፈጨፈና ህዝቡን እያፈናቀለ ስላለው የመሬት ሽያጭና ነጠቃ የክልሉ እጅ የለበትም ብለዋል። ሂይውማን ራይትስ ዎች ባለፈው ሳምንት ባወጣው ሪፖርት ላይ በክልሉ ስለሚካሄደው የመሬት ነጠቃ አቶ በረከት ስምኦን በበኩላቸው ምላሽ ሲሰጡ በክልሉ ከሶስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ባለቤት የሌለው መሬት መኖሩን መናገራቸው አይዘነጋም።**

እሳቸው የሚወለዱበት የአኙዋክ ብሄረሰብ ንጹሃን ዜጎች ላይ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ የአቶ መለስን ስም በመጥራት አብረው እንደሚጠየቁ በግምገማው ወቅት ስለመናገራቸው ለተጠየቁት "በጭራሽ" የሚል ማስተባበያ የሰጡት አቶ ኦሞት ጭፍጨፋው ሲከናወን በወቅቱ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር እንደነበሩና የተጨፈጨፉትን ንጹሃኖች የግድያ ዝርዝር ማዘጋጀታቸውን በስደት ላይ ያሉት የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኦኬሎ አክዋይ መናገራቸው ተጠቅሶ ሰፊ ማብራሪያ እንዲሰጡበት አለመደረጉ ግራ ያጋባ ጉዳይ ሆኗል።

ቃለምልልሱን አስመልክቶ አስተያየት የሰጡ እንዳሉት አቶ ኦሞት አንድም መስቀለኛ ጥያቄ እንዲቀርብላቸው አለመደረጉ ብዥታን ፈጥሮባቸዋል። በሌላም በኩል በክልሉ ግምገማ ወቅት ፕሬዚዳንቱ የተናገሩት ቃል የድምጽ መረጃ ያላቸው ክፍሎች ለማስተባበያው ምላሽ ለመስጠት በዝግጅት ላይ እንደሆኑ ፍንጮች እየታዩ ነው።

ለጉዳዩ ቅርበት ያለቸው አንድ የክልሉ ከፍተኛ የስራ ሃላፊ አቶ ኦሞትን ከቀድሞው የቤኒሻንጉል ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ያረጋል አይሸሹ ጋር አመሳስለዋቸዋል። ሲያብራሩም አቶ ያረጋል በከፍተኛ ሙስናና ወንጀል የሺናሻ ብሄረሰብ አባል በሆኑት ምክትላቸው በተደጋጋሚ ክስ ሲቀርብባቸው፣ የፌደራል መንግስት ከለላ የሚሰጠው ለአቶ ያረጋል ነበር።

አቶ ያረጋል አስፈላጊነታቸው እስኪያበቃ ድረስ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወሩ ተደረገ። የፌደራሉ የማህበራት ማደራጃ ኮሚሽነር ሆነው ተሾሙ። ካናዳ ለህክምና ሄደው ኮበለሉ ከተባለ በኋላ በተመሳሳይ ማስተባበያ አቅርበው አገር ቤት ተመለሱ። በመጨረሻም በከፍተኛ የሙስና ወንጀል እንዲጠየቁ ለማመቻቸት ያለመከሰስ መብታቸው ተነሳ። እንደ ሃላፊው ማብራሪያ ጊዜው ሲደርስ እስር ቤት ወረዱ።

አሁንም እየሆነ ያለው ተመሳሳይ ጉዳይ መሆኑን የገለጹት ሃላፊው አቶ ኦሞት ካገር እንዲወጡ ከቶውንም እድል እንደማይሰጣቸው ተናግረዋል። የቅርብ የህወሃት ምንጫቸውን በማስረጃነት በመጥቀስ የተናገሩት እኚሁ አስተያየት ሰጪ ምክንያታቸውንም አብራርተዋል። "አቶ ኦሞት ካገር ከወጡ አቶ መለስና መንግስታቸው ላይ ምስክር ይሆናሉ። አቶ ኦሞት ከተሰደዱ በአካል ለዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ምስክርነታቸውን መስጠት ግዳጃቸው በመሆኑ የህወሃት ሰዎች ስጋት አለባቸው። ስለዚህ አቶ ኦሞት በተቀመጠላቸው የስድስት ወር የሃላፊነት ዘመናቸው አድርጉ የተባሉትን እየፈጸሙ ይኖራሉ። የህወሃት ሂሳብ ይህ ቢሆንም በመጨረሻ ያልታሰበ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል እገምታለሁ። ምክንያቱም ነገሮች ተነካክተዋል" በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

ለጊዜው ከፓርቲ ሊቀመንበርነታቸው የተነሱት አቶ ኦሞት ስድስት ወር በፕሬዚዳንትነታቸው ስለመቀጠላቸው ለተጠየቁት እርግጠኛ ሆነው አልመለሱም። የአሜሪካ ሬዲዮ እንግዳ ሆነው ጥር 11 ቀን 2004 ዓም የቀረቡት አቶ ኦሞት ያነጋገረቻቸው ጋዜጠኛ ትዝታ በላቸው ነበረች። ፕሬዚዳንቱ ዘገባዎችን ሲያስተባብሉ "ስሜን ለማጥፋት የተነሱ" በማለት በተደጋጋሚ ለተናገሩት ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሚዲያና ህዝብ ግንኙነት አቶ ኦሞት "የሚጠፋ ስምና ማንነት የላቸውም። የሚያስጨንቀን የሳቸው ስም ሳይሆን በግፍ የተጨፈጨፉ ወገኖቻችንና ንብረታቸውን በግፍ እየተዘረፉ ያሉት ዜጎች ጉዳይ ነው" ብሏል። አያይዞም ያሉትን መረጃዎች በማጠናከር ዝርዝር መረጃ ይፋ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ አስታውቋል።

በተያያዘ ዜና ሰሞኑን ይፋ የተደረገውን የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ለማስተባበል ተግባር የሚውል ዶክመንታሪ ፊልም እንዲዘጋጅ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ከፍተኛ አመራሮች መመሪያ መስጠቱን ምንጮቻችን ተናግረዋል።

ምንጮቻችን እንዳሉት የሚዘጋጀው የማስተባበያ ፊልም በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን በፊልሙ መንግስትን እያሞካሹ አስተያየት እንዲሰጡ የተመረጡ የበታች አመራሮችና ምስኪን ገበሬዎች የሚናገሩትን እንዲያጠኑ ይደረጋል። ለቀረጻው ውበት ያመች ዘንድ ወፍጮ ቤቶችና ክሊኒኮችን ቀለም የመቀባትና የማስዋብ ስራ እንዲሰራ ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

ከወራት በፊት ቢቢሲ ላቀረበው አስደንጋጭ ዘገባ ምላሽ ለመስጠት ገንዘብ የተከፈላቸው ሰዎች ተዘጋጅተው የቢቢሲን ዘገባ እየተቃወሙ እንዲናገሩ መመሪያ እንደተሰጣቸው በተለያዩ መገናኛዎች መዘገቡ አይዘነጋም። በቢቢሲ ዘገባ ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል አርሶ አደሮች በረሃብ እንዲቀጡ መደረጋቸውና በኦጋዴን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ የተፈፀመውን አስነዋሪ ግፍ

ሰለባዎችን በምስል በመቅረጽ ማቅረቡ አይዘነጋም። በተመሳሳይ አሁን እንዲሰራ መመሪያ የተላለፈበት ዘጋቢ ሪፖርቱ "አኬልዳማ ቁጥር ሁለት" ተብሎ በዋልታ ኢንፎርሜሽን ሰራተኛ ስም እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሏል።

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

---

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

